# የእውነታ ዝርዝር —አጠቃላይ መረጃ
(በሌላ ቋንቋዎችም ቀርቧል)

## የጡት ነቀርሳ ምንድን ነው?

የጡት ነቀርሳ ያለማቋረጥ የሚያድግና የሚባዛ የተዛባ የህዋስ ጥርቅም ነው። ከጊዜ በኋላ እነዚህ ህዋሳት በጡት ውስጥ ወደ እባጭነት ይለወጣሉ። ይህ ነቀርሳ ተቆርጦ ካልወጣ ወይንም ቁጥጥር ካልተደረገበት ነቀርሳው በመላው አካል በመዛመት ቀስ በቀስ ለሞት ሊዳርግ ይችላል።

## የጡት ነቀርሳ ይይዘኛል ብዬ መስጋት ይኖርብኛል ወይ?

በአውስትራሊያ ከስምንት ሴቶች ውስጥ አንዷ በሕይወት ዘመኗ ጊዜ በጡት ነቀርሳ ትያዛለች።

**በጡት ነቀርሳ ለመያዝ ዋናው የችግሩ ምክንያት ሴት መሆንና ከ50 ዓመት በላይ መሆን ነው።**

## የበሽታ ማጣሪያ ማሞግራም ማለት ምንድን ነው?

የበሽታ ማጣሪያ ማሞግራም ያልተዛባ ወይንም ምንም ለውጥ በሌለበት የሴት ጡት ላይ የሚደረግ የዝቅተኛ ጨረር የራጅ ምርመራ ነው። የበሽታ ማጣሪያ ማሞግራም ምርመራ 90% የሚሆነውን ነቀርሳ፤ በመነካካት ለማግኘት የማይቻለውንም ጨምሮ፤ መለየት ያስችላል። **ቀድሞ ከተገኘ ለመከላከል በጣም ጥሩ ነው።** ነቀርሳውን በቅድመ ደረጃው መለየት በህክምና ለመዳን የሚኖረውን እድል ከፍ ያደርገዋል።

## የማጣሪያውን ምርመራ በየስንት ጊዘው ማድረግ አለብኝ ?

እድሜአቸው 50 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሴቶች፤ በየሁለት ዓመቱ የበሽታ ማጣሪያ ማሞግራም ቢያደርጉ ይመረጣል። ይሁንና፤ በአንዳንድ ምክንያቶች የበሽታ ማጣሪያ ማሞግራም በየዓመቱ ማድረጉ ሊመረጥ ይችላል።

## የበሽታ ማጣርያ ማሞግራም ምርመራ በነፃ ነው?

‘BreastScreen WA’ በምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ በመንግሥት የገንዘብ እርዳታ ስለሚካሄድ **ነፃ** የማሞግራም ማጣሪያ ምርመራ በየሁለት አመቱ እድሜአቸው ከ50 እስከ 69 ዓመት ለሆኑ ሴቶች ይደረጋል። እድሜአቸው በ40 እና 49 መካከል እንዲሁም ከ70 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶች በጥያቄ ነፃ የማሞግራም ማጣሪያ ምርመራ በምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ በኩል ማግኘት ይችላሉ። እድሜአቸው ከ40 ዓመት በታች ለሆነ ሴቶች በምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ በኩል የማሞግራም ማጣሪያ ምርመራውን ማግኘት አይችሉም።

## የማሞግራም ማጣሪያ ምርመራውን ከየት ማግኘት እችላለሁ?

በምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ በከተማ ውስጥ ሰባት አገልግሎቶች አሉት። እነሱም፤ ካኒግተን፤ ፍሪማንትል፤ ጁንዳለፕ፤ ሚድላንድ፤ ሚራቡካ፤ በፐርዝ ከተማና ሮኪንግሃም ናቸው። በተጨማሪም በየክፍለ ሃገሩ እየተዘዋወሩ በየሁለት ዓመቱ አገልግሎት የሚሰጡ አራት ተንቀሳቃሽ ክሊኒኮች አሉ።

## ‘BreastScreen WA’ በምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያን በምጎበኝበት ጊዜ ምን ይከሰታል?

ወደ ምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ አገልግሎትን በሚመጡበት ጊዜ፤ አንድ ወጥ የሆነ ልብስ ከመልበስ ይልቅ፤ **ሸሚዝና ቀሚስ ወይንም ሸሚዝና ሱሪ ቢለብሱ ይመረጣል። በተጨማሪም ምንም አይነት የጠረን መከላከያ አይቀቡ።** በምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ ድርጅት ሲደርሱ የሚከተሉት ሂደቶች ይከናወናሉ፡

1. እንኳን ደህና መጡ ይባሉና የግል ዝርዝር ሁኔታዎንና ፈቃደኛነትዎን የሚጠይቅ ቅጽ እንዲሞሉ ይደረጋል
2. ፒጃማ ከለበሱ በኋላ ሴት የራዲዮግራፊ ባለሙያ ወደ ራጅ ክፍል ትወስድዎትና ጥቂት ጥያቄዎች ታቀርብልዎታለች። ከዚያ በኋላ እያንዳንዱን ጡትዎን ሁለት ጊዜ ራጅ ታነሳለች።
3. የራዲዮግራፊ ባለሙያዋ የተነሱትን ራጅ የቴክኒክ ጥራቱን እስክትመረምር ድረስ እንዲጠብቁ ይጠየቃሉ።
4. የራዲዮግራፊ ባለሙያዋ ምርመራው ስለማለቁም ሆነ መቼ መሄድ እንደሚችሉ ትነግርዎታለች።
5. የራጅ ምርመራው ቢያንስ በሁለት የልዩ ባለሙያ ዶክተሮች ከታየ በኋላ ውጤቱ በ14 የሥራ ቀኖች ውስጥ ይላክልዎታል።
6. ሴቶችን ለሁለተኛ ጊዜ ለራጅ ምርመራ መጥራት አዲስ ነገር አይደለም። ይህ አስፈላጊ ከሆነ ከምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ የጡት ግምገማ ነርስ ስልክ ደውላ ታወያይዎታለች፡

## የማሞግራም የማጣራት ሥራ የሚደረገው እንዴት ነው?

ራጅ በሚደረግበት ጊዜ በራጅ ማንሻው መሳሪያ ላይ ጡቱ በትክክል ከተቀመጠ በኋላ ራጅ እስኪደረግ ድረስ ለጥቂት ሰኮንዶች በጣም በመጫን ይያዛል። እያንዳንዱ ጡት ሁለት ጊዜ፤ ማለትም፤ ካላይ አንድ ከታች አንድ ጊዜ ይነሳል። የመጫኑ ሁኔታ ጠበቅ ስለሚል አይመች ይሆናል ነገር ግን ማመም የለበትም። ይሁንና በተቻለ መጠን ጥራት ያለው ፎቶግራፍ ለማንሳትና አነስተኛ የራጅ ጨረር ለመጠቀም፤ የመጫኑ ሂደት በጣም አስፈላጊ ነው። (ከዚህ በታች የተመለከቱትን ፎቶግራፎች ይመልከቱ)






*ጡቱን ሳይጫኑ የሚነሳው ራጂ ደብዛዛ ይሆናል።*

*ጡቱን በመጫን የሚነሳው ራጂ የጠራ ይሆናል።*

## በማሞግራም የማጣራት ምርመራ ማድረጉ ለምን ያስፈልጋል?

**ቀድሞ በሽታውን ማግኘቱ ጥሩ የመከላከያ ዘዴ ስለሆነ ነው። የበሽታ ማጣሪያ ማሞግራም ምርመራ ሕይወትዎን ያድናል።**

## በስልክ ቁጥር 13 20 50 ደውሎ ቀጠሮ መያዝ ይቻላል።

በነፃ የማስተርጎም አገልግሎት ከፈለጉ እባክዎን በቅድሚያ ለትርጉም አገልግሎት (TIS) በስልክ ቁጥር 13 14 50 ደውለው፤ ከምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ ማእከላዊ የቀጠሮ መያዣ አገልግሎት ጋር በስልክ ቁጥር 13 20 50 ጋር እንዲያገናኙዎት ይጠይቁ።

## በቡድን ቀጠሮ ስለመያዝ

በቡድን ለመቅረብ ለሚፈልጉ ሴቶች በቡድን ቀጠሮ የሚያቀናጅ አገልግሎት አለ። ለምሳሌ አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሴቶች፤ የአንድ ክለብ ወይንም ማህበር ወይንም ጓደኞች፤ በቡድን ቀጠሮ መያዙ አመቺ ሊሆን ይችላል። በቡድን ቀጠሮ ስለመያዝ ተጨማሪ ጥያቄ ካለዎት እባክዎን በስልክ ቁጥር 13 20 50 ይደውሉ።

## ነፃ መረጃ

ስለ ጡት ማጣሪያ ምርመራ፤ ስለ ጡት ነቀርሳ፤ በቤተሰባቸው መካከል የጡት ነቀርሳ ታሪክ ላላቸው ሴቶች፤ ጡታቸውን በቀዶ ጥገና ላስተካከሉ ሴቶች፤ ስለጡት ህመም፤ ለአካለ ጎደሎ ሴቶችና ሌላም ሌላም በርካታ የነፃ የጡት ማጣሪያ ምርመራ መረጃ አለ።

## በሌላ ቋንቋ የሚገኝ መረጃ

'For Me and My Family' (video) ለእኔና ለቤተሰቤ የሚል ቪዲዎ በአረብኛ፤ በካንቶኒስ፤ በክሮኤሽያን፤ በእንግሊዝኛ፤ በግሪክኛ፤ በጣልያንኛ፤ በካመር፤ በመሴዶንያን፤ በራሽያንኛ፤ በፖሊሽ፤ በሰርቢያን፤ በስፓኒሽ፤ በታጋሎግ፤ በቱርክኛ እና በቪየትናሚዝ ቋንቋ ተጽፎ ይገኛል።

'General Information - Fact Sheet' ይህ አጠቃላይ መረጃ - የእውነታ ዝርዝር፤ በእንግሊዝኛ፤ በአማርኛ፤ በአረብኛ፤ በቦዝንያን፡ በበርሚስ፤ በቻይኒስ፤ በክሮኤሽያን፤ በዳሪ፤ በፋርሲ፤ በግሪክኛ፤ ኢንዶኔሽያን፤ በጣልያንኛ፤ በመሴዶንያን፤ በማሌ፤ በሞልቲስ፤ በኔዘርላንድኛ፤ በካመር፤ በፖሊሽ፤ በፖርቹጊስ፤ በሰርቢያን፤ በሶማሊ፤ በስፓኒሽ፤ በሱዋሂሊ፤ በታጋሎግ፤ በታይ፤ በትግርኛ በቪየትናሚዝ ቋንቋ ተጽፎ ይገኛል።

'After your screening mammogram - What next?' ከ 'ማሞግራም ማጣርያ ምርመራ በኋላ - ምን ይከተላል? የሚለው የእውነታ ዝርዝር በእንግሊዝኛ፤ በአረብኛ፤ በቦዝንያን፤ በቻይኒስ፤ በክሮኤሽያን፤ በዳሪ፤ በግሪክኛ፤ ኢንዶኔሽያን፤ በጣልያንኛ፤ በመሴዶንያን፤ በማሌ፤ በፖሊሽ፤ በፖርቹጊስ፤ በሰርቢያን፤ በስፓኒሽ እና በቪየትናሚዝ ቋንቋ ተጽፎ ይገኛል።

'Screening Mammography for Women with a Family History of Breast Cancer' የጡት ነቀርሳ ታሪክ ላለባቸው ሴቶች፤ የማሞግራፊ የማጣሪያ ምርመራ በእንግሊዝኛ፤ በቦዝንያን፤ በቻይኒስ፤ በዳሪ፤ በማሌ፤ በሰርቢያን እና በቪየትናሚዝ ቋንቋ ተጽፎ ይገኛል። '

**መረጃዎችን ማዘዝ ከፈለጉ እባክዎን በስልክ ቁጥር 9323 6762 ይደውሉ ወይንም በኢሜል** breastscreenwa@health.wa.gov.au